# ለእግዚአብሔር ፍቅር

"… እኔ የሚረባህን ነገር የማስተምርህ በምትሄድባትም መንገድ የምመራህ አምላክህ እግዚአብሔር ነኝ።" (ኢሳ 48 ÷ 17)
God's Love, P.O.Box 6734 , Lee's Summit, MO, 64064. / E-mail – mtizazu@hotmail.com / Ph/Fax 816 – 246 – 9395

ነሐሴ 1995 August 2003 "ልጆችሽም ሁሉ ከእግዚአብሔር የተማሩ ይሆናሉ ፡ የልጆችሽም ሰላም ብዙ ይሆናል።" (ኢሳ 54÷13)

www.EthioGodslove.org

"እናንተ የዓለም ብርሃን ናችሁ። በተራራ ላይ ያለች ከተማ ልትሰወር አይቻላትም። መብራት አብርቶ እንቅብ የሚደፋበት ማንም የለም። ይልቅስ በቤት ውስጥ ላሉት ሁሉ እንዲያበራ ብርሃኑ በሚታይበት በከፍተኛ ቦታ ላይ ያደርገዋል። እንዲሁም ሰዎች መልካም ሥራችሁን አይተው የሰማይ አባታችሁን እንዲያመሰግኑት የእናንተም ብርሃን በሰው ፊት ይብራ።" (የማቴዎስ ወንጌል 5÷14-16 አዲሱ ትርጉም)

## የሚታይ ምስክርነት



አንድ አይሁድ ባልና ሚስት የመጀመሪያ ልጃቸውን ሲወልዱ በልጁ ስያሜ ላይ መግባባት ተሳናቸው። ብዙ ከተከራከሩ በኋላ ካሕኑ (ረቢው) መጥተው እንዲገላግሉአቸው ጠሩ።

ካሕኑም ተጠርተው በመጡ ጊዜ "ችግራችሁ ምንድን ነው? ሲሉ ባልና ሚስትን ጠየቋቸው። ሚስቲቱም ቀድማ በመናገር፡-"መምሕር ሆይ፡- ባሌ ልጃችንን በአባቱ ስም መሰየም ይፈልጋል። እኔም ደግሞ በአባቴ ስም እንዲሰየም እፈልጋለሁ።" አለች። ከዚያም መምሕሩ"የአባትህ ስም ማን ይባላል?" ሲሉ ባልየውን ጠየቁት።ባልየውም "ዮሴፍ" ሲል መለሰ። ቀጥሎም ሴትየዋን "የአንቺስ አባት ማን ይባላል? ሲሉ ጠየቋት፤እርስዋም "ዮሴፍ" ስትል መለሰች።

ካሕኑም በመገረም፡- "ታድያስ ጥላችሁ ምኑ ላይ ነው?" ብለው ሲጠይቁ፡- አሁንም ሚስቲቱ ቀደም በማለት፡- "መምሕር ሆይ ችግራችን ቀላል አይምሰልዎ፤የባሌ አባት ዮሴፍ ፈረስ ሰርቆ ተይዞ ነበር። የእኔ አባት ዮሴፍ ግን በጻድቅነቱ ሐገር ያወቀው ሰው ነበረ። እንግዲህ ልጃችን በጻድቁ በአባቴ ስም መሰየሙ እንዴት ይታወቃል?" ስትል ችግሯን አብራራች።

ከዚያም (ረቢው) መምሕሩ ትንሽ ካሰቡ በኋላ "ልጃችሁን ዮሴፍ በሉት። ከዚያም ልጁ እያደገ ሲሄድ፡- የፈረስ ሌባ ወይም ጻድቅ ሰው መሆኑ እየተገለጠ ይመጣል። በዚያንም ጊዜ የማንኛችሁን አባት ስም እንደወሰደ ይታወቃል።" ሲሉ አስታረቋቸው።

ራሳችንን ጻድቅና የእግዚአብሔር ሰው አድርገን ማሰብ አንድ ነገር ሲሆን አካሄዳችን በየዕለቱ የሚመለከቱ ሰዎች፡- "የእግዚአብሔር ሰው" ቢሉን ግን ፈጽሞ የተለየ ነገር ነው።

አንድ ጊዜ የአሲሲው ቅዱስ ፍራንሲስ የተባሉት መነኮሴ፡- እንደ ልማዳቸው ከገዳሙ ወጥተው ወደ ከተማ ለስብከት ሲወጡ÷ አንዱን ወጣት መነኮሴ አብሯቸው እንዲሄድ ለመኑት። ወጣቱም መነኮሴ ከታዋቂው የእግዚአብሔር ሰው ጋር ለመውጣት በመታደሉ ተደሰተ።

ከዚያም ሁለቱ ተከታትለው ወደ ከተማው አመሩ። ከተማም እንደ ደረሱ ÷ አውራውን መንገድ እየተከተሉ ከዳር እስከ ዳር ተጓዙ። ከሚያጋጥማቸው ተላላፊ ሁሉ ጋራ ፈገግታና ሰላምታ እየተለዋወጡ በከተማው ተዘዋወሩ።

ብዙም ከተዘዋወሩና ከተማውን ካዳረሱ በኋላ በሌላ መንገድ አድርገው ወደ ገዳማቸው ተመለሱ። በዚህን ጊዜ ወጣቱ መነኮሴ ፍራንሲስ የዘነጉት የመሰለውን ነገር ሊያሳስባቸው፡- "አባቴ÷ ከገዳም የወጣነው ለመስበክ እንደ ነበረ ረስተዋል"አላቸው። ፍራንሲስም መልሰው "ልጄ ሰብከናል እንጂ አልረሳንም። በብዙ ሰዎች ታይተናል። አካሄዳችንና ግብረ ገብነታችን ታይቶአል። ባሕሪያችን በብዙዎች ተመዝኖአል። እየተነጋገርን ስንጓዝ ንግግራችን በአንዳንዶች ጆሮ ገብቶአል። እኛ መነኮሴዎች አንዳንድ ጊዜ የማለዳ ስብከታችንን የምንሰብከው በዚህ መልክ ነው" ሲሉ መለሱለት።

መጥምቁ ዮሐንስ ለጌታ ኢየሱስ የሚመሰክር ድምጽ እንደ ነበረ ከመጽሐፍ እናነባለን። ነገር ግን ድምጽ ብቻ አልነበረም። ሕይወቱም (ኑሮውም) እንደ ድምጹ ነበረ። ሰው የአፉ ቃልና አኗኗሩ ሲጋጭ ሕይወቱ ለውጥን ማስከተሉ እንደማይቀር ከዮሐንስ መማር ይቻላል በዚሁ አንጻር አምናለሁ የሚሉትን በተግባር የማይኖሩበት ሰዎች ደግሞ ሕይወታቸው የማያንጽና ፍሬ አልባ ሲሆን አዘውትሮ ይታያል። በአጠቃላይ ክርስትናችን የሚመለከቱንን ሰዎች ሊማርክ የሚችለው÷ በኃይማኖት መልካችን ወይም በአገልግሎት ማዕረጋችን ሳይሆን፤ በየዕለቱ በሕብረተ ሰቡ መሐከል በምንመላለስበት ሕይወታችን (አካሄዳችን) ነው። እንዲሁም ከሆነ፡- ሕይወታችን ስማችንን ይወስናል እንጂ ስማችን የሕይወታችን ጥሩ አመልካች አይሆንም።

"እንዲሁም ሰዎች መልካም ሥራችሁን አይተው የሰማይ አባታችሁን እንዲያመሰግኑት የእናንተም ብርሃን በሰው ፊት ይብራ" (ማቴ 5÷16 አ/ት)

(ማክስ ለኬዶ Gentle Thunder በሚል ከጻፈው መጽሐፍ ተወስዶ ከተዘጋጀ መልዕክት የተተረጎመ)

## ቅብዓት ቅዱስ

"እግዚአብሔር ሙሴን እንዲህ አለው÷... ምርጥ የሆኑ ቅመሞችን÷... ውሰድ... እንደ ሽቶ ቀላቅለህ የተቀደሰ የቅባት ዘይት ሥራ፤እኔ የምመለክበትን ድንኳን÷ ... ለመቀባት ተጠቀምበት። በዚህ ዓይነት እነዚህን ሁሉ በመለየት ፍጹም የተቀደሱ ታደርጋቸዋለህ። ... ይህ የተቀደሰ የቅባት ዘይት ለሚመጡት ዘመናት ሁሉ ለእኔ አገልግሎት ይዋል፤" (ዘጸአት 30÷22-31)

በብሉይ ኪዳን ሥርዓት እግዚአብሔርን በክሕነት የሚያገለግሉት ከሕዝቡ ተለይተው የተመረጡ ሰዎች ብቻ ነበሩ። እነርሱም እግዚአብሔርን በሚያገለግሉበት ጊዜ÷ከላይ በተጠቀሰው መሠረት በተዘጋጀ ቅዱስ ዘይት ተቀብተው ይቀደሱ ነበር። የዘይቱን አሠራር ለሙሴ የነገረው እግዚአብሔር ራሱ ስለ ሆነ፡- በዕውነት ክብርና ቅዱስ÷ለእግዚአብሔር ክብር ብቻ መዋል ያለበት ቅዱስ ዘይት ነው።

ከኦሪት ዘጸአት 30÷22 ጀምሮ ስለ ቅዱስ ቅባት የተመለከተውን ስናጠና የምንረዳው÷ ዛሬ በቤተ ክርስቲያን የሚሠራውን መንፈስ ቅዱስን ነው። መንፈስ ቅዱስ ለእግዚአብሔር መንግሥት አገልግሎት ይለየናል። በብሉይ ኪዳን የቤተ መቅደሱ ዕቃዎችና ካሕናቱ በቅዱስ ቅባት ይቀደሱ እንደ ነበሩት÷በአዲስ ኪዳን ደግሞ÷የወንጌሉን አገልጋዮች ይቀድስና የአገልግሎት ኃይል ይሆነን ዘንድ መንፈስ ቅዱስ ተሰጥቶናል። እግዚአብሔር ይመስገን።

ቅባቱ ልዩነት ያደርጋል። ሕዝቡ በፈርዖ እግዚአብሔር ከኃጢአት እየራቀ በዕውነትና በመንፈስ ቅዱስ የሚያመልክበት ቤተ ክርስቲያን ልዩነት አለው። እንደዚህ ባለ ቤተ ክርስቲያን አጋንንት የያዛቸው ሰዎች ቢመጡ አጋንንቱ ይለቅቃቸዋል። የታመሙ ሲጸለይላቸው ይፈወሳሉ። ኃጢአት ያደረገ ይቅርታ ቢፈልግ ይሰረይለታል። የእግዚአብሔር ሕልውና ይገለጻል። ስለዚህም የእግዚአብሔር ሕዝብ በአሕዛብ ፊት የተፈራ ይሆናል። እግዚአብሔርም እንደሚገባው ይከብራል። እግዚአብሔር ይመስገን።

በዘመናት ሁሉ ውስጥ አምላካችን እግዚአብሔር ክብሩን የሚገልጡትን ፈቃዱንም የሚፈጽሙትንና በቅድስና ከእርሱ ጋር የሚሄዱትን ሰዎች ሲለይ ኖሮአል። መንፈስ ቅዱስ የአዲስ ኪዳን ቅብዓት ቅዱሳችን ነው። በመንፈስ ቅዱስ ሳንቀደስ እግዚአብሔርን በዕውነት ማወቅም÷ማምለክም÷ማገልገም አንችልም። ምክንያቱም እርሱ አስተማሪአችን ነው፡- "...አብ በስሜ የሚልከው ግን መንፈስ ቅዱስ የሆነው አጽናኝ እርሱ ሁሉን ያስተምራችኋል፤ እኔም የነገርኋችሁን ሁሉ ያሳስባችኋል።" ስለሚል ነው። (ዮሐ 14÷26)

ያለ መንፈስ ቅዱስ ስግደታችን ከንቱ ነው። "ነገር ግን በዕውነት የሚሰግዱ ለአብ በመንፈስና በዕውነት የሚሰግዱበት ጊዜ ይመጣል፤አሁንም ሆኖአል፤አብ ሊሰግዱለት እንደ እነዚህ ያሉትን ይሻልና፤እግዚአብሔር መንፈስ ነው÷የሚሰግዱለትም በመንፈስና በዕውነት ሊሰግዱለት ያስፈልጋቸዋል።" (ዮሐ/ ወ/ 4÷23-24)

## መንፈስ ቅዱስን መቀበል

ኢየሱስ ክርስቶስን ጌታዬና አዳኜ ብሎ በዕውነት አምኖ በመቀበል ይጀምራል። በዚህ ጊዜ በተዓምራዊ የመለኮት አሠራር መንፈስ ቅዱስ ወደ ልብህ ገብቶ መሥራት ይጀምራል።

ማንም ሰው ከልቡ በዕምነት የሚከተለውን ዓይነት ፀሎት ሲፀልይ፡- (ቢታወቀውም ባይታወቀውም)መንፈስ ቅዱስ ይሰርጸዋል (ወደ ልቡ ይገባል)፡፡ ይህ የታወቀ የእግዚአብሔር አሠራር ነው፡፡ ሰው የእግዚአብሔር የደኅንነት ስጦታ የሆነውን ኢየሱስን ሲቀበል፥ የእግዚአብሔር ልጆች አሳዳጊ፥መሪና አስተማሪ የሆነው መንፈስ ቅዱስ ወደዚያ ሰው መምጣት ተግባሩ ነው፡፡ ከዚያ በኋላ የማደጋችን ሁኔታ የሚወሰነው፡- ከኃጢአት በመራቃችንና ለእግዚአብሔር ቃል በመታዘዛችን መጠን ላይ ይሆናል፡፡

ደኅንነትን ካገኘን በኋላ ግን እግዚአብሔርን እያወቅነው ስንሄድ እጅግ ስለ ምንወደው፥ መንፈስ ቅዱስንም ዘወትር ስለምንጠማ፥ለመንፈስ ቅዱስ ሙላት ወደ መፀለይ እንሸጋገራለን፡፡እግዚአብሔርም በመንፈስ ቅዱስ ያጠምቀናል፡፡ (ይሞላናል፡፡) ልዩነት አለ፡፡ *<u>የመንፈሱ መስረጽ የመዋጀት መለያ ሲሆን፡- የመንፈስ ቅዱስ ሙላት (ጥምቀት) ደግሞ ሙሉ በሙሉ በጌታ ቁጥጥር ውስጥ የመዋል መለያ ነው</u>*፡፡ ያመነ ሁሉ መንፈስ ቅዱስ ሰርጾታል፡፡ ያመነ ሁሉ ግን በመንፈስ ቅዱስ የተሞላ አይደለም ማለት ነው፡፡ እግዚአብሔር ሁሉንም ሰጥቶናል፡፡ቅብዓት ቅዱሱ (መንፈስ ቅዱስ) ሊሰርጽህም ሊሞላህም ተፈቅዶአል፡፡ ደኅንነትን ተቀብለሃል? በመንፈስ ቅዱስ ተጠምቀሃል?

# የደኅንነት ፀሎት

ጌታ እግዚአብሔር ሆይ፡- ስለ ኃጢአታችን የሞተውንና ከሙታን ያስነሣኸውን ልጅህን ኢየሱስን ለደኅንነቴ አምኜ እቀበላለሁ፡፡ ከዛሬ ጀምሮ እርሱ ጌታዬ ነው፡፡ አንተም አምላኬ ነህ፡፡ ከኃጢአት ርቄ እኖራለሁ፡፡ አንተም በመንግሥትህ ተቀበለኝ፡፡ አሜን፡፡

# ቅብዓት ቅዱስ

## የመንፈስ ቅዱስ ሙላት

ጌታ እግዚአብሔር ሆይ፡- እኔ ልጅህን ኢየሱስን አምኜ ተቀብየዋለሁ፡፡ ስለዚህ "… መንፈስ ቅዱስ በእናንተ ላይ በወረደ ጊዜ ኃይልን ትቀበላላችሁ፥… እስከ ምድር ዳርም ድረስ ምስክሮቼ ትሆናላችሁ" (የሐ/ ሥራ 1፥8) በሚለው ቃልህ መሠረት፥ለአገልግሎትህ ብቁ እንዲያደርገኝ፡- በመንፈስ ቅዱስህ ሙላኝ፡፡ እኔም ከኃጢአት ርቄ በመኖር እጠነቀቀለታለሁ፡ ፀሎቴን ስለ ሰማህልኝ አመሰግንሃለሁ፡፡ በጌታ በኢየሱስ ስም፡፡ አሜን፡፡

⟷

# የቅብዓት ቅዱስ ሕግ

**የሚሰጠው ለአገልግሎት ነው፡-**

"በክሕነትም *<u>ያገለግሉኝ ዘንድ</u>* አሮንንና ልጆቹን ቀባቸው፥ቀድሳቸውም፡፡ (ዘጸዓት 30፥30)

"… መንፈስ ቅዱስ በእናንተ ላይ በወረደ ጊዜ ኃይልን ትቀበላላችሁ…እስከ ምድር ዳርም ድረስ *<u>ምስክሮቼ ትሆናላችሁ</u>*" (ሐዋ ሥራ 1፥8)

**መንፈስ ቅዱስን ማስመሰል የተረገመ ነው፡፡**

"*<u>እንደ እርሱ ያለውን የሚያደርግ ሰው</u>*፥ በሌላም (በማይገባው) ሰው ላይ የሚያፈስሰው *<u>ከሕዝቡ ተለይቶ ይጥፋ</u>*፡፡" (ዘጸዓት 30፥33)

መንፈስ ቅዱስ ከኃጢአት ጋር ተዳብሎ መኖር ስለማይችል፡- ኃጢአትን ካልተውን ሊወሰድብን ይችላል፡-

ለዚህ ነው ፥ የእግዚአብሔር ሰው ዳዊት "ከፊትህ አትጣለኝ፥ ቅዱስ መንፈስህንም ከእኔ ላይ *<u>አትውሰድብኝ</u>*" ሲል የጸለየው፡፡ (መዝ 51፥11)

---

## የመጽሐፍ ቅዱሳችን ክፍሎች



## ብሉይ ኪዳን፡- (39 መጽሐፎች)

### የሕግ መጽሐፎች፡-

አሪት ዘፍጥረት
አሪት ዘጸአት
አሪት ዘሌዋውያን
አሪት ዘኍልቍ
አሪት ዘዳግም

### የታሪክ መጽሐፎች (History)

መጽሐፈ ኢያሱ
መጽሐፈ መሳፍንት
መጽሐፈ ሩት
መጽሐፈ ሳሙኤል ቀዳማዊና ካልዕ
መጽሐፈ ነገሥት ቀዳማዊና ካልዕ
መጽሐፈ ዜና መዋዕል ቀዳማዊና ካልዕ
መጽሐፈ ዕዝራ
መጽሐፈ ነህምያ
መጽሐፈ አስቴር

### የመዝሙር መጽሐፎች(poetry)

መጽሐፈ ኢዮብ
መዝሙረ ዳዊት
መጽሐፈ ምሳሌ
መጽሐፈ መክብብ
መኃልየ መኃልይ ዘሰሎሞን

### አብይ ነብያት (major prophets)

ትንቢተ ኢሳይያስ
ትንቢተ ኤርምያስ
ሰቆቃወ ኤርምያስ
ትንቢተ ሕዝቅኤል
ትንቢተ ዳንኤል

### ንዑስ ነብያት (minor prophets)

| | |
|---|---|
| ትንቢተ ሆሴዕ | ትንቢተ ናሆም |
| ትንቢተ አሞጽ | ትንቢተ ዕምባቆም |
| ትንቢተ ሚክያስ | ትንቢተ ሶፎንያስ |
| ትንቢተ ኢዮኤል | ትንቢተ ሐጌ |
| ትንቢተ አብድዩ | ትንቢተ ዘካርያስ |
| ትንቢተ ዮናስ | ትንቢተ ምልክያስ |

## አዲስ ኪዳን መጽሐፎች

(27 መጽሐፎች)

### ወንጌል

የማቴዎስ ወንጌል
የማርቆስ ወንጌል
የሉቃስ ወንጌል
የዮሐንስ ወንጌል

### ታሪክ

የሐዋሪያት ሥራ

### የቅዱስ ጳውሎስ መልዕክቶች

ወደ ሮሜ ሰዎች
ወደ ቆሮንቶስ ሰዎች 1ኛ እና 2ኛ
ወደ ገላትያ ሰዎች
ወደ ኤፌሶን ሰዎች
ወደ ፊልጵስዩስ ሰዎች
ወደ ቈላስይስ ሰዎች
ወደ ተሰሎንቄ ሰዎች 1ኛ እና 2ኛ
ወደ ጢሞቲዎስ ሰዎች 1ኛ እና 2ኛ
ወደ ቲቶ
ወደ ፊልሞና

### አጠቃላይ መልዕክቶች፡-

(general letters)

ወደ ዕብራውያን
የጴጥሮስ መልዕክት 1ኛ እና 2ኛ
የዮሐንስ መልዕክት 1ኛ፥2ኛ፥3ኛ
የያዕቆብ መልዕክት
የይሁዳ መልዕክት

### የትንቢት መጽሐፍ

የዮሐንስ ራዕይ፡፡

**********

ውድ አንባቢዎቻችን ከዚህ በላይ ያነበባችሁትን ያቀረብነበት ምክንያት የመጽሐፍ ቅዱስን ክፍሎች አበክሮ ማወቅ ለሚፈልጉት እንዲረዳ ነው፡፡ ይህ የአንድ ጊዜ ንባብ አይደለም፡፡ ደጋግሞ በማንበብ የሚሸመደድ እንጂ፡፡ በመጽሐፍ ቅዱስ ጥናትና በሰንበት ትምሕርትም ወቅት ለጥናት ይረዳል፡፡

❖❖❖❖❖❖❖❖❖❖

# የዌብ ገጽ

# WEB PAGE

www.EthioGodslove.org

ይህ የዌብ አገልግሎታችን ገጽ ነው፡፡ ኢንተርኔት ያላችሁ፡-ደብዳቤአችንን ማንበብም ፥ ማተምም ትችላላችሁ፡፡ ፊደል ሊኖራችሁ ግድ አይደለም፡፡ ከዚህ በፊት ያስታወቅነው www.gods-love-ethiopia.com ስለ ረዘመ ለውጠነዋል፡፡ ሆኖም አሁንም ይታያል፡፡

**********

# እስፖንሰር

አፍሪካ ለሚኖሩት አንባቢዎቻችን እስፖንሰር በመሆን የፖስታ ዋጋ የምትረዱን ወገኖች ጌታ ይባርካችሁ፡ እያልን፡- ርዳታችሁን በየዓመቱ እንድታደርጉ በትሕትና እናሳስባችኋለን፡፡ 12 ዓለም አቀፍ የፖስታ ቴምቤር ብትልኩልን ለዓመት ይበቃናል፡፡ በገንዘብ ወይም በቴምቤር ላኩልን፡፡ ትልቁ ወጪአችን የፖስታ ቴምቤር ነው፡፡

እህት ኤልሳቤጥና ወንድም አሰፋ አብዲ፡ ከዋሽንግተን ዲሲ፡ የላካችሁልን ቸርነት ደርሶናል፡፡ ጌታ በምትፀልዩበት ሁኔታ ላይ ቸርነቱን ፈጥኖ ይግለጥላችሁ፡፡ አሜን፡፡

ምክር፥ ጥያቄ ወይም አስተያየት ብትጽፉልን በጣም እናመሰግናለን፡፡ አድራሻችን፡-

God's Love
P O Box 6734
L. S. MO 64064 USA ወይም
mtizazu@hotmail.com

---

"አስተምርሃለሁ፡ በምትሄድበትም መንገድ እመራሃለሁ፥ ዓይኖቼን በአንተ ላይ አጸናለሁ፡፡" (መዝ/ዳዊት 32፥8)

ኢየሱስ ጌታ ነው፡፡ ጌታ ይባርክህ፡፡